የኤፈርት ፍጻሜ፣
የኢትዮጵያን ለኢትዮጵያዊያን?

የደብረጽዮን ሮኬትና የተማጽኖ ደብዳቤ
አሁንስ የኦነግ ሸኔ ተስፋ ማን ነው?

በጡት ነካሾች ምክንያት
- መስዋዕትነት እንደገና


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ቅጽ 2 ቁጥር 110 ህዳር 2013 ዓ.ም

ዋጋ 20.00




በተለይ ለግዮን

## “ቴዎድሮስ አድኃኖም የእስር ትዕዛዝ ሊወጣበት ይገባል”

“ጆባይደን የኢትዮጵያን ሕልውና የሚፈታተን ነገር ያደርጋል ብዬ አላምንም”

ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም

# ግዮን ክፍል ፩


ክፍል አንድ
1-24

ክፍል ሁለት
25-28

"ኑ አብረን እንሙት" የትህነግ የፍጻሜ ፊሽካ! 2

5 የኤፈርት ፍጻሜ፣ የኢትዮጵያን ለኢትዮጵያዊያን?

ረቂቅ የዘመኑ ጦርነት! 12
ዳግም ግዛቸው

"ዋናው ዓላማችን ሴቶች ገበያቸውን አስፋፍተው መሥራት እንዲችሉ ማድረግ ነው" 14
ወ/ሮ እንግዳዬ እሸቱ

የጦርነቱ ተጋድሎዎች 17

21 ትግራይ ውስጥ ያለው መሠረታዊ ችግር ምንድን ነው?
መታሰቢያ መልዓከሕይወት

ተጠያቂዉ ማን ይኾን? 22
በቀለ ቆልቻ (ከወላይታ ሶዶ)

በጡት ነካሾች ምክንያት - መስዋዕትነት እንደገና 23
ሠሎሞን ለማ ገመቹ.

ዜና 3



"ቴዎድሮስ አድኃኖም የእስር ትዕዛዝ ሊወጣበት ይገባል"
"ጀባይደን የኢትዮጵያን ሕልውና የሚፈታተን ነገር ያደርጋል ብዬ አላምንም"
ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም
8

የችግሩን ምንጭ ከማድረቅ ጎን መዋቅራዊ ለውጥ እንሻለን! 4

ማኅበራዊ ሚዲያ 13

አንደበት 16





ቁጥር 109

ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ህዳር 26/2013 ዓ.ም
ይጠብቁን

# “ቴዎድሮስ አድኃኖም የእስር ትዕዛዝ ሊወጣበት ይገባል”

## “ጆባይደን የኢትዮጵያን ሕልውና የሚፈታተን ነገር ያደርጋል ብዬ አላምንም”

ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም



ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም በሃገረ-አሜሪካ ሳን ቤርናርዲኖ የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ናቸው፡፡ በሥነመንግሥት፣ ሲቪል መብትና በአሜሪካ ሕገመንግሥት ዙሪያ ዳሰሰ ያሉ ጥናቶች በማድረግ የሚታወቁት ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም፣ በአፍሪካ በተለይም ደግሞ በኢትዮጵያ ይስተዋል የነበረውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ ላለፉት ዐሥራ ሦስት ዓመታት በተከታታይ ጦማሮችን በማዘጋጀት ለዓለማ አቀፉ ማኅበረሰብ የአገዛዙን ባህሪ ሲያጋልጡ ቆይተዋል፡፡ በኢትዮጵያ ከኹለት ዓመት በፊት የመጣውን ለውጥ ተከትሎ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ የአማካሪዎች ካውንስል ዋና ሊቀመንበር በመኾን ከማስተማር ሥራቸው ጎን ለጎን ሀገራቸውን የሚያገለግሉት ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያምን፣ ስለሕይወታቸው፣ ስለኢትዮጵያ አጠቃላይ ፖለቲካዊና ነባራዊ ጉዳዮች የሚከተለውን ሰፊ ቆይታ ከጋዜጠኛ ፍቃዱ ማኅተመወርቅ ጋር አድርገዋል፡፡ የመጀመሪያውን ክፍል እንኾ!

**ግዮን፡- የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ዶናልድ ትራንፕ የሕዳሴ ግድቡን በተመለከተ በተናገረው ንግግር በምርጫው አሸናፊ እንዳይኾን ኢትዮጵያውያን የሠሩት ሥራ ቀላል አይደለም ይባላል፡፡ የእርሶ ሚና ደግሞ በጣም የገዘፈ ነው የሚሉ ወገኖች አሉና ምን ይላሉ በዚህ ዙሪያ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ ግልፅ በኾነ መንገድ ዶናልድ ትራንፕን ተሟግቸዋለሁ፤ ታግየዋለሁም፡፡ እስከ ምርጫው መጨረሻም “ትራንፕ ዩሮፋግ” የሚል ሰፋ ያለ ጽሑፍ አቅርቤ ከነማስረጃው ሕገ መንግሥቱን እንዴት እንደጣሰው ወንጀለኛ ነው በሚል አስቀምጫለሁ፡፡ በአጭሩ በእኔ እምነት ትራንፕ ማለት ወያኔ ማለት ነው፡፡ በዘር የሚከፋፈል፣ ጥላቻ የሚነዛ ግለሰብ ነው፡፡ ስለዚህ ይኽ ሰው የወያኔ አምሳል ነው፡፡ ስለዚህ የትራንፕ ንግግር ኢትዮጵያ ላይ ጦርነት ማወጅ ነው፡፡ በጎንዮሽ ኢትዮጵያ ላይ ጦር ነው የሰበቀው፡፡ ይኽን አድሎ የጀመረው ዛሬ ሳይሆን ከዓመት በፊት ሕዳር ስድስት ነበር፡፡ ይኸውም ኢትዮጵያውያንን “ኑ ላደራድራችሁ” ብሎ እዚያው አታልሎ እጅ ጠምዝዞ ለማንበርከክ ነበር የፈለገው፡፡ ይኽም ከአልሲሲ ጋር ተስማምተው ያደረጉት ነው፡፡ እኔ ደግሞ ይኼን ነገር ተከታትዬ በየጊዜው በተለያዩ መልኩ ስትራቴጅው ምን እንደኾነ ሳስረዳና ሳሳውቅ ነበር፡፡

ይኽን ሊያደርጉ ነው፣ ይኽን እየፈጠሩ ነው፣ በማለት በተለይ እርዳታ ሊያቆሙ እንደሚችሉ፣ ዓለም ባንክ ብድር እንደሚከለክል ወዘተ በሙሉ በግልፅ አስገንዝቤ ነበር፡፡ እንደውም ለገንዘብ ሚኒስትሩ የጻፍኩት ላይ እነዚህን ነገሮች በሙሉ በደንብ አስፍሬያለሁ፡፡ ትክክል በኾነ መንገድ ጀምረው ኢትዮጵያን ለማንበርከክ ያደረጉትን ጥረትና መጨረሻ ላይ ደግሞ እንደማይሰራላቸው ተናግሬ ነበር፡፡ ስለዚህ ከትራንፕና መሰል አካላት ጋር ያለኝ ጦርነት ከግል ጦርነት ያልተለየ ስለኾነ ለረጅም ጊዜ የተካሄደ ነበር፡፡ በርግጥ አንዳንዴ ደግሞ ትራንፕ መልካም ነገሮችን ሲያደርግ ከመደገፍ አልቦዘንኩም፡፡ ለምሳሌ 2017 ላይ ሥልጣን ▶

እንደያዘ በተለይ ለአፍሪካ ሀገራት የሚለግሱትን ገንዘብ በተመለከተ የሚሰሩበትን ነገር ሳናጣራ ለሙስና ማስፋፊያ ገንዘብ አንሰጥም ማለታቸውን ደግፌ ነበር፡፡ ስለዚህ ትራንፐ ከእርዳታችን ጎን ለጎን ሙስናውን እንመለከታለን ሲል ከባድ ድጋፍ ሰጥቼዋለሁ፡፡ በኋላ ግን ወራት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ነገሩን በሙሉ አበላሸው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት የኦባማ መንግሥት በቀጥታም ባይኾን በእነ ሱዛን በኩል የወያኔ ደጋፊ መኾኑ ይታወቃል፡፡ ትራንፐ ደግሞ ኦባማ ሠራ የተባለውን ነገር በሙሉ ማጣጣልና ማጥፋት ስለሚፈልግ ለወያኔ ተቃዋሚዎች ወይም ለእኛ የተመቸ ጊዜ ነበር፡፡ በዚህም ለወያኔ በኦባማ ደረጃ የሚታይ ምንም ዐይነት እርዳታ አልሰጠም፡፡ ነገር ግን ኢትዮጵያ ላይ ይኽንን ንግግር በማድረጉ ጦርነት እንዳወጀ ነው የምቆጥረው፡፡ ስለዚህ ለዚህ ሰውዬ መልስ መስጠት የሚቻለው እርሱን ከሥልጣኑ በማባረር ነው፡፡ በመኾኑም በግሌ ያደረግኩት አንደኛው ጥረት በተለይ ኢትዮጵያውያኖች በተለያዩ ግዛቶች(ስቴትስ) ያሉትን የሞት ሞታችሁን ኾናችሁ ወጥታችኹ ምረጡ እያንዳንዷ ድምጽ ታስፈልጋለች፡፡ ምክንያቱም ኹለት ሺህ ላይ ቡሽ ያሸነፈው ጠቅላላ በአምስት መቶ ድምጽ ነው፡፡ ስለዚህ በተቻላቸው አቅም ወጥተው እንዲመርጡ መቀስቀስ ነው፡፡ ቅስቀሳዬ ደግሞ በጽሑፍና በአንዳንድ ፎረሞች ላይ ሃሳቦቼን በማራመድ ነበር፡፡ በተጨማሪም ለዲሞክራቶች የሚኾን ብዙ ገንዘብን አሰባስበን፡፡ በግላችንም፣ በድርጅትም ደረጃ፣ የእነርሱንም ሰዎች አካተን በተቻለን መጠን እንዲያውቁን እና እንደረዳናቸው እንዲያውቁ በማድረግ ቅስቀሳውን አደረግን፡፡ ይኽ በመሆኑም ባይደን ሥልጣኑን ተቆጣጠረ፡፡ እንግዲህ በምንም ዓይነት መልኩ ባይደን ወጥቶ የኢትዮጵያ ግድብ ይደበደባል እንደማይል ባለሙሉ ዕምነት ነኝ፡፡ ሰውዬው እንደዚህ ዓይነት ቅሌት የለበትም፡፡ ለግብጽም ወግኖ ኢትዮጵያን ያጠቃል ብዬ እንደዚህ ግልጽ በኾነ መንገድ አላስብም፡፡ ኢትዮጵያ ላይ ጦር አዝምቱ አይልም፡፡ ነገር ግን ትራንፐ ይኽን ያደረገበትን ምክንያት ሳስብ እ.ኤ.አ 2016 ለሥልጣን ሲወዳደር ምርጫው መጨረሻ ላይ ከግብጽ ወደ 10 ሚሊዮን ብር ለእርሱ መቀስቀሻ ተልኮ ነበር፡፡ የዚህን ውለታ ለመመለስ ያደረገው ነው ብዬ እንድገምት እገደዳለሁ፡፡ ግብፅ 10 ሚሊዮን ብር መስጠቷ ደግሞ በብዙ መልኩ የተረጋገጠ ነው፡፡ ይኼ ደግሞ አሁን ከሥልጣን ከወረደ በኋላ በሕግ የሚጣራ ይኾናል፡፡ ይኽን ያደረጉት ደግሞ በግድቡ በኩል ኢትዮጵያን እንዲያንበረክኩላቸው ነው፡፡ ስለዚህ እኛ ደግሞ ይኽን የትራንፐን ከግብፅ ጋር መወገን ማምከኛችን በምርጫ መጣል ነበርና ዲሞክራቶች እንዲያሸንፉ ትንሽም ቢኾን በቅስቀሳው አስተዋጽዖ አድርገናል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

**ግዮን፡- ከአዲሱ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት (ከጆባይደን) ለኢትዮጵያ ምን የተለየ ነገር ይጠብቃሉ? ከአሜሪካ ፖሊሲ ይወጣል ብለው ያስባሉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እንደሚታወቀው አሜሪካ ሁልጊዜ የራሷን ጥቅም ነው የምታስጠብቀው፡፡ ነገር ግን ትራንፐና ባይደን የተለያዩ ሰዎች ናቸው፡፡ ሰማይና ምድር ማለት ናቸው፡፡ ትራንፐ የውጪ ፖሊሲ የለውም፡፡ በዘፈቀደ የሚሰራ ግለሰብ ነው፡፡ አያነብም፣ እልም ያለ መሀይም ነው፣ ከእርሱ ምንም የሚጠበቅ ነገር የለም፡፡ ባይደን ግን በሴኔቱ ውስጥ ከ40 በላይ ዓመታትን ሰርቷል፡፡ ምክትል ፕሬዝዳንት ኾኖ ደግሞ ስምንት ዓመት አገልግሏል፡፡ የበሰለ ሰው ነው፡፡ የሚሰራውን የሚውቅ ግለሰብ ነው፡፡ የዲፕሎማሲ ጉዳዮችን ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው፡፡ ስለዚህ አስተማማኝ መንገድ ነው የሚፈልገው፡፡ በእርግጥ ልክ ኦባማን እንደተጠቀሙበት አንዳንድ ሰዎች ተጠቅመው ኢትዮጵያ ላይ ወያኔን ለመርዳት ብለው የሚያደርጉት ተጽዕኖ ሊኖር ይችላል፡፡ ግን እንደምገምተው አሁን ላይ መሸጋገሪያ ከመንግሥት ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ትራንፐ ዝም ብሏል፡፡ ትራንፐ እስከመጨረሻው ዝም ይላል የሚል ግምት አለኝ፡፡ ስለዚህ እነርሱ ተዘጋጅተው ይኽንን ነገር አትኩረው በቲውተር ከመጻፍ በስተቀር የሚያደርጉት ነገር የለም፡፡ የሰብዓዊ ጥሰት አይፈጠር፣ ሰው አይሙት የሚል አቋም ካልኾነ ባይደን ኢትዮጵያ ላይ የተሻለ አስተያየት ይኖረዋል ብዬ ነው የምገምተው፡፡ ለዚህ ደግሞ ብዙ ምክንያቶችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አፍሪካ ቀንድ አካባቢ የአልሸባብን መንሰራፋት አይሹም፡፡

ኢትዮጵያ ጠንካራ ካልኾነች ከባቢው በሙሉ ያልተረጋጋ ይኾናል፡፡ ቀጣናው ካልተረጋጋ ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ ላይ እንደነቦኮሃራም ሊፈነጩ ነው ማለት ነው፣ ይኽን ደግሞ አይፈቅዱም፡፡ በዚኽም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መልካም ግንኙነትን ይመሠርታሉ፡፡ በሌላ ጎኑ ትራንፐ ሲል የነበረውን ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ ላይ ጫና እናሳርፋለን ነበር የሚለው፡፡ ጫና ማለት የዓመት ችሮታ አንሰጥም ነው፣ ከዓለም ባንክ የምታገኙትን እናስቀንሳለን ነው፡፡ በዲፕሎማሲ በኩል አንዳንድ ነገር እንዳታደርጉ ተጽዕኖ እናደርጋለን ነው፡፡ ሌላ ትራንፐ ሕግ የማያከብር ሰው ነው፡፡ ሕግ የማያከብረው ትራንፐ ማድረግ ያልቻለውን ነገር ባይደን ሊያደርግ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ትራንፐ ሞከረ፣ ዕርዳታ አቆምኩ አለ፣ ኹለት መቶ ስድሳ ሚሊዮን ብር አቆመ፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ደግሞ እሺ ከቆመ ቆመ ምንም ችግር የለም ብሎ ዝም አለው፡፡ ከዚህ ሌላ ምንድነው ምንም ሊያደረግ አልቻለም፡፡ ባይደንም ቢኾን ከዚያ የተሻለ ነገር በዲፕሎማሲ በኩል ለማድረግ ይሞክራል እንጂ ይኽን የትራንፐን ፖሊሲ ተከትሎ የኢትዮጵያ ሕልውና የሚፈታተን ነገር ያደርጋል ብዬ አላምንም፡፡ ሁላችንም ልንገነዘበው የሚገባው የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ በትራንፐ፣ በባይደን፣ በዩኤስ ኮንግረስ የሚወሰን አለመኾኑን ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብና በኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው፡፡ ይኽንን በደንብ አድርገን ማረጋገጥ አለብን፡፡ ለሦስት ሺህ ዘመን ነፃነታችንን ያስጠበቅነው የነጮችን ወይም የአውሮፓውያንን እግር እየሳምን አይደለም፡፡ እንደውም አውሮፓውያን እኛ ጋር መጥተው ሊያንበረክኩን ሲሉ አስተምረን የላክናቸው ነን፡፡ በአድዋ ቢባል በሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ ቀደም ባሉት ዘመናት ግብጽ ለመውረር በሞከረች ጊዜ ሁሉ በራሳችን አቅም በመተማመን መክተናል፡፡ ስለዚህ እኛ የምንቀጥለው እኛ በወሰንነው ውሳኔ ብቻ ነው፡፡ በርግጥ ከውጭ ብዙ ተጽዕኖ ሊያደርሱብን ይችላል፡፡ እነዚያ ተጽዕኖዎች ምናልባት የኢትዮጵያን ልማታዊ ግስጋሴ ሊያዘገዩት ይችሉ ይኾናል፡፡ ግን መጨረሻ ላይ መደርሳችን አይቀርም፡፡ ይኽንን ሁሉ ትግል አልፈን መጨረሻ ላይ ስንደርስ ለአፍሪካ ጮራ ነው የምንኾነው፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያን ተመልከቷት፣ ያ ኹሉ ተጽዕኖ ደርሶባት፣ ያ ጫና ተደርጎባት ሊያሸንፏት አልቻሉም፡፡

ሦስት ሺህ ዘመን ነጻነቷን አስጠብቃ ቅኝ ሳትያዝ እስከዛሬ የደረሰችበት የራሷ ምክንያት አላት፡፡ በእኔ እምነት ኢትዮጵያውያን በጣም ልዩ ሕዝቦች ነን፡፡ ኢትዮጵያ ከሌላው የምትለይባቸው ብዙ ማሳያዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ከ40 ጊዜ በላይ ተጠቅሳለች፣ ነብዩ መሐመድ ተከታዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ሒዱ እዚያ ጥሩ አገር ጥሩ መንግሥት አለ ኢትዮጵያን አትንኩ ብለው የተናገሩባት ሀገር ናት፡፡ የአፍሪካ ሕብረት የተቆረቆረባት ሀገር ኢትዮጵያ ናት፣ የመንግሥታቱ ድርጅት ሲመሠረት ግንባር ቀደም መሥራቿ ኢትዮጵያ ናት፡፡ በ1940ዎቹ

**እኛ የምንቀጥለው እኛ በወሰንነው ውሳኔ ብቻ ነው. በርግጥ ከውጭ ብዙ ተጽዕኖ ሊያደርሱብን ይችላል.**

**እነዚያ ተጽዕኖዎች ምናልባት የኢትዮጵያን ልማታዊ ግስጋሴ ሊያዘገዩት ይችሉ ይኾናል**

**ግን መጨረሻ ላይ መደርሳችን አይቀርም**

**ይኽንን ሁሉ ትግል አልፈን መጨረሻ ላይ ስንደርስ ለአፍሪካ ጮራ ነው የምንኾነው**

**ምክንያቱም ኢትዮጵያን ተመልከቷት፣ ያ ኹሉ ተጽዕኖ ደርሶባት፣ ያ ጫና ተደርጎባት ሊያሸንፏት አልቻሉም . . .**

ገደማ፣ በዓለም ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ነበረች፡፡ ከአፍሪካ ሀገራትም ትለያለች፣ ከሌላውም ዓለም እንዲሁ፡፡ ስለዚህ እኛ እራሳችንን አለማወቃችን እንጂ ከዓለም የተለየንና ገናና ማንነት ያለን ኩሩ ሕዝቦች ነን፡፡ ሁሌ እኛ የምንዳከመው ራሳችን በራሳችን እንጂ ማንም የውጭ ኃይል በግሮን አይደለም፡፡ ይኽን ደግሞ እኔ ሳልኾን ታሪክ ምሥክር ነው፡፡ ወደኋላ ዞረን እንመልከት እስቲ፣ ግራኝ አሕመድ ሞከረ ጠፋ፣ ጣሊያን ሞከረ ጠፋ፣ ፖርቱጋሎች ሞከሩ ጠፉ፣ እንግሊዞች አጼ ቴዎድሮስ ላይ ሞከሩ ጠፉ፣ ግብጾች ሞከሩ ጠፉ፡፡ ከውጭ ያሸነፈን ኃይል የለም፡፡ ስለዚህ የሚያጠፋን የራሳችን ጥላቻና የራሳችን አለመተማመን ብቻ ነው፡፡



**ግዮን፡- በቅርቡ በሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሠራዊት ላይና በማይካድራ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ዘግናኝ ጭፍጨፋ መካሄዱ የሚታወስ ነው፡፡ እርሶ ይኽን ሁነት በተመለከተ ነገሩን ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ለመውሰድ እየተንቀሳቀሱ ነውና ስለሂደቱ ቢነግሩን?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ያው የፍርድ ነገር ሲመጣ መረጃ ዋናው ነው፡፡ ማይካድራ ላይ እስካሁን ያለኝ መረጃ የሚጠቁመው የጦር ወንጀሎች ተፈፅመዋል የሚል ነው፡፡ የጦርነት ወንጀል ሲባል ደግሞ በየትኛውም ዓለም ላይ ኾነ በአገሩም ሕግ ይመስለኛል ወንጀለኛ መቅጫ ላይ "ዘር ማጥፋት" የሚባል የወንጀል ዓይነት እናዳለ አውቃለሁ፡፡ ይኽ የወንጀል ዓይነት የሚለው አንድ ጦርነት ሲካሄድ ወይም ግጭት ሲኖር ንጹሐኑ መነካት የለባቸውም፡፡ አንድ የሚሸሽ ጦር እየሸሸ ያንን መከላከል ሲያቅተው ንጹሐኑን እየጨፈጨፈ ከሄደ የጦር ወንጀል ነው፡፡ ንጹሐንን መንካት አይቻልም፡፡ በኑረንበርግ ሕግም ኾነ ብዙ ዓለም አቀፍ ሕጎች አሉ፡፡ በዓለም አቀፍ የወንጀል ሕግም ቢኾን የሮም ድርድር በሚባለው በዚያም ላይ የተመዘገበ ነው፡፡ ማይካድራ ላይ ከሕግ አንጻር እኔ የተመለከትኩት ከ500 ሰዎች በላይ በታጠቁ ኃይሎች ጄኖሳይድ እንደተፈጸመባቸው ነው፡፡ የተፈፀመው ነገር ደግሞ ዘር ተኮር ስለሆነ በጄኖሳይድ ያስከስሳል፡፡ ስለዚህ ሦስት ዓይነት የክስ ቻርጅ ይኖርባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ዘር ማጥፋት ሲሆን ኹለተኛው ደግሞ የጦር ወንጀል ነው፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ "crime againest humanty" የሚባለው ወንጀል ነው፡፡ ሦስተኛው የወንጀል ዓይነት የሰቆቃውን ዓይነትና መጠን የሚገልፅ ነው፡፡ ማለትም ሰው ደብድበዋል፣ ንብረት አውድመዋል፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ገድለዋል፣ የሰውን ሰብዓዊ መብት ገፈዋል ወዘተ… የሚለውን የሚገልፅ ነው፡፡ ስለዚህ ወንጀለኞቹ በዚህም ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ብዙ ሰዎችን እየጠለፉ መውሰድም በዓለም አቀፍ ሕግ የሚያስጠይቅ ነው፡፡ ለምሳሌ ከራያ አካባቢ ከ10 ሺህ የሚልቁ እስረኞችን የሰወሩበት ሂደት ራሱን የቻለ ወንጀል ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በጦር ሠራዊቱ ላይ የፈፀሙት ወንጀል በዓለም ሕግ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ ነው፡፡ በትኛውም ቦታና ሀገር እጅ የሰጠ ኃይል ላይ እርምጃ አይወሰድም፡፡ እንደውም መጠነኛ የኾነ እንክብካቤ ይደረግለትና ይቀመጥ ነው የሚለው ፤ የዓለም ሕግ፡፡ በማይካድራ በኩልም የተጨፈጨፉ ወገኖች ስም ዝርዝር ይፋ ቢኾን መልካም ነው፡፡ እዚህ ላይ እናንተም ብትተባበሩኝ ደስ ይለኛል፡፡ ያ ሲኾን ነው ፍርድ ቤት ይዞ መቅረብ የሚቻለው፡፡ በዚህ ጉዳይ ማስረጃውን ይዘን ከቀረብን ዐቃቢ ሕጉ ነፃ በኾነ መልኩ ይኽን ወንጀል መመርመር ይችላል፡፡ የተሰጠውን ማስረጃ ወስዶ ለኢትዮጵያ መንግሥት ያቀርብና እነዚህን ሰዎች ያዝዋቸው፡፡ አለዚያ እኛ ሕጋዊ እርምጃ እንወስዳለን የሚል መልዕክትም ያስተላልፋል፡፡ የዓለም አቀፍ ወንጀል ሕግ የሚወስዳቸው እርምጃዎች የአንድ አገር መንግሥት አልችልም ሲል ወይም የስምምነቱ አባል ሳይኾን ሲቀር ነው፡፡ ለምሳሌ ኬንያ የዚያ ስምምነት አካል ስለነበረች ባለፈው ምርጫ በተፈጠረው ችግር ተጠይቀውበታል፡፡ ኢትዮጵያ ግን የዚህ ስምምነት አካል አይደለችም፡፡ ግን በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት "international crime court" ይመልከትልኝ የማለት ሙሉ መብት አለው፡፡ ስለዚህ ጉዳዩ በኹለት መንገድ ሊታይ ይችላል፡፡ አንዱ እኛ በግለሰቦች ወይም በሲቪክ ማህበራት ደረጃ ጉዳዩን ለ"ICC" ፕሮስኪውተር ዐቃቢ ሕግ ማቅረብ እንችላለን፡፡ የኢትዮጵያ መንግሥትም ማቅረብ ይችላል፡፡ ነገር ግን ይኽንን ለማድረግ የማቾች ሙሉ መረጃ ሊኖረን ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተደረገውን አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታ ማካተት አለብን፡፡ ይኽን ለማድረግ ደግሞ በእናንተ በኩልም በኢሜል መረጃዎችን ብታደርሱን ለእኛ ትልቅ እርዳታ ነው፡፡ በተለይ አሁን ላይ ጉዳት የደረሰባቸው አካባቢዎች ኢንተርኔትና ስልክም ስለሌለ መረጃዎች እየደረሱኝ አይደለም፡፡ ያው ይኽን ደግሞ መናገር ያለበት በዓይኑ ያየ ሰው ሊኾን ስለሚገባ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል፡፡ በእርግጥ ሚዲያዎች ሲዘግቡ ቪዲዮ ላይ የተናገሩትን መረጃ አስቀምጨዋለሁ፡፡ ከተቻለን በቪዲዮ ያየናቸውን ሰዎች መርማሪዎችን ልከን ሰዎቹን እንዲያነጋግሩ ለማድረግ እንሞክራለን፡፡

**ግዮን፡- ህወሓት በዚህ ደረጃ ራሱን አዘጋጅቶ ጦርነት ይከፍታል ብለው አስበው ነበር? የጦርነቱን አካሄድስ እንዴት አዩት?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እነሱ ጦርነት የመክፈት ችሎታ የላቸውም፡፡ ምክንያቱም በዓለም አቀፍ ሕግ ጦርነት ሊከፍት የሚችለው አንድ ሀገር በሌላ ሀገር ላይ ነው፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ሕገመንግሥት በግልፅ የተቀመጠ ነገር አለ፡፡ ምክር ቤቱ ወይም ኮንግረሱ ብቻ ጦርነት ከፍቷል ብሎ በሕግ መወሰን አለበት፡፡ ጦርነት ማለት ሕጋዊ እርምጃ ነው፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካና በቬትናም መካከል የተደረገው ጦርነት "ጦርነት" አይደለም፡፡ ምክንያቱም ኮንግረሱ የወሰነው እና የመከረበት ስላልሆነና የአሜሪካ ፕሬዝዳንቶች በስሜት የጀመሩት ስለሆነ ሕጋዊ እርምጃ አይደለም፡፡ ያም ራሱ በሕገመንግሥታዊ መንገድ ከታየ "ፖሊሲ አክሽን" ተብሎ ነው የሚታየው፡፡ ስለዚህ ይኽ ጦርነት በኮንግረሱ እውቅና የሌለው ወታደራዊ እርምጃ ነው፡፡ ኢራቅ ደግሞ አፍጋኒስታንን ስትጋብዝ ኮንግረሱ ጦርነት አላወጀም፡፡ የኃይል መጠቀም ሥልጣን ነው የሰጠው፣ ለፕሬዝዳንቱ፡፡ የኒውክሌር ቦንብ እያዘጋጁ ነው፣ ሽብርተኞች መሽገዋል በሚል

ነው አገሪቱን እንዲያረጋጋ ፕሬዝዳንቱ የተፈቀደለት፡፡ ስለዚህ መንግሥት ብቻ ነው ጦርነትን ሊከፍት የሚችለው፡፡ ወያኔዎች ደግሞ መንግሥት አይደሉም፣ የክልል አስተዳዳሪዎች እንጂ፡፡ የክልል አስተዳደር ወታደራዊ እርምጃ ከወሰደ መንግሥትን ተቃወመ እንጂ ጦርነት ከፈተ አይባልም፡፡ እነሱ ያደረጉት ግን የሽብር ተግባር መፈፀም ነው፡፡ ቀደም ሲል TPLF አሸባሪ እንደሆነ ገልጬ ነበር፡፡ ስለዚህ አሸባሪ ጦርነት ሊከፍት አይችልም፡፡ አሸባሪ ሽብር ብቻ ነው መፍጠር የሚችለው፡፡ የህወሓቶችን ሽብር ለየት የሚያደርገው 27 ዓመት በሕገወጥ መንግሥትነት በመቆየታቸው መሳሪያ አከማችተው ድርጅታዊ ቅርፅ ለመያዝ አስችሏቸዋል፡፡ አልሻባብም በሥልጣን ላይ ኖሮ ይኽን ተግባር ቢፈጽም ያው ነው፡፡ እነርሱም የሠሩት የአልሸባብን ሥራ ነው፡፡ ለምሳሌ ኤርትራ ላይ ሮኬት ተኮሱ፡፡ ይኼ የሽብር ሥራ ነው፡፡ ለምሳሌ አሜሪካን አገር 2001 ላይ ሃያ የሚኾኑ የሳውድ ዐረቢያ አሸባሪዎች መጡ፡፡ ትልቅ ሕንጻ አጥፍተውም ሦስት ሺህ ሰዎችን ገደሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ሰዎች አሜሪካ ላይ ጦርነት ከፍተዋል ማለት ነው? አልከፈቱም፡፡ እዚያ ላይ የሞተውና ከዚያ ጥቃት ጋር የተያያዘው ነገር በሙሉ ዘጠኝ ዐሥራ አንድ የሽብር ጥቃት ነው የሚባለው፡፡ በእኛ ሀገር የተፈጸመውንም በግሌ "የሕዳር ሃያ አራት የሽብር ጥቃት" ብዬ ነው የማምነው፡፡

ግዮን፡- ከሕግ አንፃር ህወሓት አሁን እያደረገው ያለው ነገር በአሸባሪነት ሊያስፈርጀው ይችላል? አሸባሪ ለመባልስ በሀገሪቱ ፓርላማ ካልፀደቀ ዓለማቀፋዊ ተቀባይነት ይኖረዋል፣ ቢያብራሩት?

ፕ/ር አለማየሁ፡- አዎ ጥያቄ የለውም፡፡ የተሻሻለው የፀረሽብር ሕግ ላይ ይኽን በተመለከተ የሚለው ነገር አለ፡፡ ለምሳሌ የመንግሥት ተቋማትን ማጥፋት የሽብር ተግባር እንደኾነ ይጠቅሳል፡፡ በዓለም አቀፍ ሕግም አንድ ሕጋዊ ያልሆነ መንግሥት በሌላው ሀገር ላይ ጥቃት ሲፈፅም ሽብር ነው፡፡ ለምሳሌ ህወሓት ኢትዮጵያን አልፎ ኤርትራ ላይ ሽብር ፈፅሟል፡፡ ይኽ ደግሞ አልሸባብ ከሶማሊያ ወጥቶ ኬንያ ላይ ከፈፀመው ጥቃት ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ስለዚህ የሀገሪቱ መንግሥት እነዚህን ሰዎች በሽብር የመጠየቅ ሙሉ መብት አለው፡፡ አምልጠው ከሀገር ቢወጡ እንኳ በኢንተርፖል በኩል በሕግ ጥላ ሥር እንዲውሉ ለማድረግ ይሞከራል፡፡ አለዚያ ደግሞ እንደ ስፔንና ኔዘርላንድ ዩኒቨርሳል ስምምነት የትም ቦታ ወንጀሉ ቢፈጸም ግለሰቡ በተገኘበት ቦታ በቁጥጥር ሥር እንዲውል ይደረጋል፡፡

ግዮን፡- ዐቃቢ ሕግ በቅርቡ በህወሓት 34 የፋይናንስ ተቋማት ላይ እገዳ መጣሉ ይታወሳል፡፡ ይኽን በተመለከተ በተለይም መንግሥት በቀጣይ ምን ማድረግ አለበት ይላሉ?

ፕ/ር አለማየሁ፡- የንብረት ጉዳይ በፍትሐብሔር የሚታይና ብዙ መንስኤ ሊኖረው የሚችል ነው፡፡ በመጀመሪያ መንግሥት ሊጠይቅ የሚችለው ድርጅቶቹ ከየት በመጣ ገንዘብ ተቋቋሙ የሚለውን ነው፡፡ ለምን ከተባለ ጥርጣሬ አለኝ ቢልና ከባንክ ተበድራችሁ አልከፈላችሁም፣ በነጻ ነው ያገኛችሁት፣ በቅናሽነው ያገኛችሁት፣ ተሰርቆ ነው የተቋቋመው የሚለውን ነገር ቢያነሳ የማጣራት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ይኽን በሚያደርግበት ጊዜ ደግሞ ማድረግ ካለበት ቅድመ ሁኔታ ውስጥ አንዱ የባንክ አካውንታቸውን ማገድ ነው፡፡ ያላቸውን ንብረት እንዳያንቀሳቅሱ ማድረግ ይችላል፡፡ ይኼ በመንግሥት ደረጃ ብቻ ሳይኾን በግለሰብ ደረጃም ማሳገድ ይችላል፡፡ ይኽ ዛሬ ብቻ ሳይኾን ከአፄ ምኒልክ ጀምሮ ሲሠራበት የነበረ ሕግ ነው፡፡ በጥቅሉ እነዚህ ሰዎች



ተቋማቱን ያገኙትና በንብረቱም የበለፀጉት ሕጋዊ ባልኾነ መንገድ ነው፡፡ ሀብቱ ያለአግባብ በጉልበት ከሕዝብ የተነጠቀ ሊኾን ይችላል፡፡ መኪናው በብድር ተገዝቶ ከባንክ ያልተከፈሉ ሊኾኑ ይችላሉ፣ ሕንፃው ተሰርቆ በመጣ ገንዘብ ተገንብቶ ሊኾን ይችላል፣ መሬቱ በፖለቲካ ውገናና በውንብድና የተያዙ ሊኾኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ብዙ ሕግ ተጥሶ የተፈራ ንብረት ስለኾነ በሕግ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ በሌላ በኩል እነዚህ ድርጅቶች ይኽን አሸባሪውን ቡድን በገንዘብና በቁሳቁስ ሲደግፉ የተገኙ የወንጀለኛ ድርጅቶች መኾናቸው ሲረጋገጥ ተቋሞቹ በሕግ ይጠየቃሉ፡፡ ይኽ ሁኔታ በኹለት መልኩ የሚታይ ነው፡፡ አንደኛው ንብረቱ ራሱ ተከሳሽ ሆኖ የሚቀርብበት ሲኾን ሌላው ደግሞ የንብረቱ ባለቤት የወንጀል ተጠያቂ የሚደረግበት አሠራር ነው፡፡ 34ቱ ድርጅቶች የማን ናቸው የሚለውም በዚህ ግምት የሚወስዱ ናቸው፡፡ እነርሱ ላይ የሚወስደውም እርምጃ ለየት ያለ ነው፡፡ ንብረቱ በፍትሐብሔር የሚታይ ሲኾን የተቋሙ አዛዥ፣ ባለቤትና ማናጀር የነበሩ ግለሰቦች ደግሞ ጉዳያቸው የሚታየው በወንጀል ነው፡፡ ምክንያቱም "ድርጅቱን ተጠቅማችሁ ይኽን ወንጀል ፈፅማችኋል" የሚለው ጥያቄ ስለሚነሳ ማለት ነው፡፡

ግዮን፡- ሰሞኑን የህወሓት ሰዎች በዓለም አቀፍ መድረክ ተጽዕኖ ለመፍጠር እየሞከሩ ነው፡፡ ይኼን ነገር እንዴት ያዩታል? በእርሶ በኩልስ በሀገሪቱ እየተካሄደ ስላለው ነገር ለዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች ለማሳወቅ የሔዱበት ርቀት ምን ይመስላል?

ፕ/ር አለማየሁ፡- ይህ በኹለት መንገድ የሚታይ ሲኾን የመጀመሪያው ህወሓት የሚያቀርበው ማወናበጃ ውጤቱ ሰውን መረበሽና ማወናበድ መኾኑ ነው፡፡ ይኽ ደግሞ ሰውን አወናብዶ በሀገር ውስጥ ለውጥ ይመጣል ብሎ መጠበቅ በተለየ መልኩ የሚታይ ነገር ነው፡፡ ዓላማው በዚህም በዚያም ጮኸው ከሕግ ተጠያቂነት ማምለጥ ነው፡፡ 27 ዓመት ሙሉ የሰሩትን ወንጀል ሽምጥጠው በድርድሩ ከተጠያቂነት ለማምለጥ የሚሰሩት ሸፋጥ ነው፡፡ ስለዚህ ይኽ እነርሱ የሚሰሩት ሥራ ይኽን ይቀይራል የሚል ዕምነት የለኝም፡፡ ይህን ያህል ጥፋት ጠፍቶ ከእነርሱ ጋር ለድርድር ሊቀመጥ የሚችል ኃይል ሊኖር አይችልም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሚታየው ደግሞ የቴዎድሮስ አድኃኖም ጉዳይ ነው፡፡ ቴዎድሮስ አድኃኖም የቀረበበትን ክስ እስካሁን አላስተባበለም፡፡ አለማስተባበሉ ደግሞ የመንግሥትን ውንጀላ ተቀብሎታል ማለት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ፡፡ ለምሳሌ ቴዎድሮስ አድኃኖም በዚህ ደረጃ ተጠያቂ እስከ ኾነ ድረስ የእስር ትዕዛዝ ሊወጣበት ይገባል፡፡ ይኽ የሚያሳየው በግለሰቡ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እየተወሰደ መኾኑን ነው፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግሥት ቴዎድሮስ አድኃኖም በሚሰራበት ተቋም በኩል ስሞታ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የሚሰራበት ተቋም አንድ አቋም ወስዶ ግለሰቡን እንዲመረምረው ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ውጭ ያለን ሰዎች ደግሞ ግለሰቡ ከሥነምግባር ያፈነገጡ ነገሮችን ሲያደርግ ለሚሰራበት ተቋም ማቅረብና እንዲመረምረው ማድረግ አለብን፡፡ በግለሰብ ደረጃም ሰውየውን መክሰስ እንችላለን፡፡ ይኽ በቀላል መልኩ የሚታይ አይደለም፡፡ በዚህ ግለሰብ ላይ ቢያንስ ዐሥር ወይም አምስት ሺህ ሰው ይመርመርልኝ የሚል ጥያቄ ቢያቀርብ ግለሰቡ ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በውጭ የሚኖረው የዳያስፖራ ምሁራን ይኽን ማድረግ ይችላል፡፡ እኔ በግሌ በዚህ ዙሪያ ለመሳተፍ ዝግጁ ነኝ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ምሁራን ከዚህ ቀደም እንዳየሁት እንዲህ ዓይነቱ ነገር ላይ ለመሳተፍ ዝግጁ አይመስሉም፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ የተወሰኑ ምሁራን እንኳ ቢሳተፉ ከጎናቸው ቆሜ ጉዳዩን ለማስኬድ ዝግጁ ነኝ፡፡ በጥቅሉ ጥቂት ሰዎችም ቢኾኑ እንቅስቃሴ ቢያደርጉ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብዬ አምናለሁ፡፡

ማስታወሻ፡- ውድ አንባቢያን ከፕሮፌሰር አለማየሁ ገ/ማርያም ጋር ያደረግነው ቆይታ በዚህ የሚገታ አይደለም፡፡ ፕሮፌሰር በአፍላ የወጣትነት ዕድሜያቸው ከኢትዮጵያ ስለወጡበት ሁኔታ፣ ወደሀገራቸው ዳግመኛ ለመመለስ 48 ዓመታት ስለምን እንደተቆጠሩ፣ ድኅረ ለውጡ ባለው የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ እና እርሳቸው ስለሚመሩት የዳያፖራ ትረስት ፈንድ ቆይታ አድርገናል፡፡ የሳምንት ሰው ይበለን፡፡

ከህወሓት በኋላስ?
አዲሱ የትግራይ ፖለቲካ ፍኖት!

ከጄነራሎቹ በሥተጀርባ

“ሀገር እና መንግሥት
ግራ የሚገባን ሕዝቦች አይደለንም”
ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ቅጽ 2 ቁጥር 111 ህዳር 2013 ዓ.ም ዋጋ 20.00




የመጨረሻው የመቀሌ ከበባ

የትግራይ አርነት እወጃ

የአዲሱ አስተዳደር የመዋቅር ዝርጋታ

## የዘመቻው መቋጫ ምዕራፍ



“በኢትዮ-ኢራን መካከል ያለውን
ሁለንተናዊ ግንኙነት ማሳደግ ተችሏል”

ዶ/ር ሳልማን ሩስታሚ (የኢራን የባህል ማእከል ኃላፊ)



“ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን
ሕገመንግሥት ቀድዶ መጣል ይኖርበታል”

“የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው”

ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም

ቅፅ 2 ቁጥር 111 ህዳር 26 ቀን 2013 ዓ.ም

ክፍል ሁለት
23-28

# ፅ
# ግዮን ክፍል

ግዮን
ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ታህሳስ 3/2013 ዓ.ም
ይጠብቁን




ቁጥር
110


ዜናዎች
ገፅ 3

አዲስ የአስተሳሰብ መንገድ
ለመከተል ወሳኙ ወቅት አሁን ነው!
2

ማህበራዊ ሚዲያ
13

ሐሙስ ቅዱስ
ወይስ እርኩስ?
7

አንደበት
16


ከህወሓት በኋላስ?
አዲሱ የትግራይ ፖለቲካ ፍኖት!
8

የዘመቻው መቋጫ
ምዕራፍ
17

“ሀገር እና መንግሥት
ግራ የሚገባን ሕዝቦች አይደለንም”
ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ
10

ከጄነራሎቹ በሥተጀርባ
21

የዶ/ር ዐቢይ እና የአፄ
የኃይለሥላሴ የባሕሪ ምስስሎሽ
መታሰቢያ መልዓከሕይወት
12



“ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን ሕገመንግሥት
ቀድዶ መጣል ይኖርበታል”
“የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው”
ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም
4

“ሥራችን ሴቶችን ማብቃት ነው”
ወ/ሮ ሮማን ደቅሲዎስ
14

# “ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን ሕገመንግሥት ቀድዶ መጣል ይኖርበታል”

## “የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው”

### ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም

በሃገረ-አሜሪካ ሳን ቤርናርዲኖ የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ከኾኑት ፕሮፌሰር አለማየሁ ገብረማርያም ጋር ከለውጡ በኋላ በሊቀመንበርነት ስለሚመሩትና የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ እንቅስቃሴ፣ ስለሕይወታቸውና በተለያዩ ሀገራዊ፣ ወቅታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከጋዜጠኛ ፍቃዱ ማህተመወርቅ ጋር ያደረጉትን ክፍል ሁለት ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ !



**ግዮን፡- ከሀገር ከወጡ ምን ያህል ጊዜ ኾኖት? በምን አጋጣሚስ ሊወጡ ቻሉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- ከሀገር የወጣሁት እ.ኤ.አ 1970 ነው፡፡ የወጣሁበት ምክንያት ደግሞ ለትምህርት ነው፡፡ በወቅቱ በ1960ዎቹና ሰባዎቹ ወደ አሜሪካ የምንሄድ ወጣቶች በጣት የምንቆጠር ስንኾን የምንወጣበት ዓላማም ለትምህርት ነበር፡፡ እኔም እድለኛ ስለነበርኩ ከሀገር ወጥቶ የመማር እድሉ ተካፋይ ኾንኩ፡፡ ያው በእኛ ትውልድ ጊዜ ልጆች ኾነን “አሜሪካ ሄደን፣ እንዲህ አድርገን፣ ይኽን ገዝተን” የሚል ምኞት ነበረን፡፡ እኔም ውስጥ ይኽ ሕልም ነበር፡፡ ምክንያቱም ብዙ የምናያቸው ብልልጭል ነገሮች ነበሩ፡፡

የመኪናው፣ የቤቱ፣ የመንገዱ፣ የልጆች የጨዋታው፣ ወጣቶቹ እንዴት በነጻነት እንደሚንቀሳቀሱ፣ የተለያዩ ሰልፎችን ሲያደርጉ ማየቱ ያስቀናንና ያጓጓን ነበር፡፡ ስለዚህም አሜሪካ መሄድ በጣም እንፈልግ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ቤተሰቦቼ ትንሽም ቢኾን ንብረት ያላቸው ስለነበሩ ለመውጣት ያን ያህል አልተቸገርኩም፡፡ በወቅቱ እማር የነበረውም ጆርጂያ በምትባለው የአሜሪካ ግዛት ውስጥ ሳንጆሴፍ በሚባል ትምህርት ቤት ነበር፡፡ ለአራት ዓመት ትምህርቴን ከተከታተልኩ በኋላ በአውሮፓውያኑ 1974 ለሦስት ወር ገደማ ወደሀገሬ ተመልሼ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ሀገሬን ላያት የቻልኩት ከ48 ዓመታት በኋላ ነሐሴ 2018 ዓ.ም ነው፡፡

**ግዮን፡- 48 ዓመት አሜሪካ ከመቆየቶ አንጻር የትምህርትና የቤተሰብ ሕይወቶ ምን ይመስል እንደነበር ቢያጫውቱኝ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- በጣም የቀለም ሰው ስለነበርኩ ከሀገሬ እንደወጣሁ ትኩረቴ ትምህርት ላይ ነበር፡፡ በተለይ በዚያን ጊዜ በአሜሪካ የሚገኙ ብዙ ወጣት ተማሪዎች የፖለቲካ አቀንቃኞች ነበሩ፡፡ እኔ ግን በወቅቱ ዝንባሌዬ ፖለቲካው ሳይኾን የመጣሁበትን ተልዕኮ ፈፅሞ ሀገርን ማገልገል ነበር፡፡ በዚህም በ1973 መጨረሻ ዲግሪዬን ከጆርጂያ ለመያዝ ችያለሁ፡፡ ወዲያውም ከፍ ሲል እንዳልኩት ለጥቂት ጊዜ ሀገሬ መጣሁና ማስተርስ ለመማር ወደ አይዋ በመሄድ አንድ ዓመት ተምሬ አጠናቀቅኩ፡፡

በመቀጠልም እ.ኤ.አ በ1976 ወደ ሚኒሶታ በመሄድ እስከ 1983 ድረስ ቆይቼ የዶክትሬት ዲግሪ (PHD) ይዣለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ በ1984 ወደ ሜሪላንድ በመሄድ ሕግ ት/ቤት በመግባት በ1988 ማጠናቀቅ ችያለሁ፡፡ እንግዲህ አብዛኛውን ጊዜዬን ያጠፋሁት በትምህርት ላይ ነበር ማለት ነው፡፡ ነገር ግን በትምህርት ላይ እያለሁም ት/ቤት ውስጥ ሥራ እሠራ ነበር፡፡ ለምሳሌ ግራጁዌት ስኩል ረዳት መምህር በመኾን ጥናት(ሪሰርች) አሠራ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ሜሪላንድ ሄድኩና ሞደርን ስቴት የሚባል ት/ቤት ተቀጠርኩ፡፡ ኹለት ዓመት አካባቢ እንደሠራሁ የሪሰርች ሴንተሩ ሰውዬ ሲሄድ እኔ አክቲንግ ዳይሬክተር ኾኜ ተሰየምኩ፡፡ በዚህ መሐል ላይም ከባለቤቴ ከምሥራቅ ገሠሠ ጋር ተዋወቅን፡፡ ከዚያ በኋላ ተጋብተንና ▶

ልጃቻችንን ይዘን ወደ ካሊፎርኒያ በመሄድ በሕግ ፍቃድ አውጥቼ በአንድ በኩል ጥብቅና እየሠራሁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ማስተማር ጀመርኩ ማለት ነው፡ ፡ በአጭሩ የቤተሰብ አመሠራረቴና የትምህርት ሕይወቴ ይኸን ይመስላል።

*ግዮን፡- ወደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ መቼ ገቡ? በተለይ ቀደም ሲል የነበሮት ሕልም ተምሮ ሀገርን ማገልገል ነበርና እንዴት የመመለስ ሀሳቦ ሊመክን ቻለ?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ ከኢትዮጵያ እንደወጣሁ ደርግ መጥቶ ዜጎችን በደፈናው መጨፍጨፍ ሲጀምር በሁሉም ነገር ተስፋ ቆርጬ ነበር። ምክንያቱም ቀደም ሲል እንዳልኩት ለሦስት ወር የመጣሁ ግዜ ለውጡን ሳይ መልካም ተስፋ ስለነበረኝ ማስተርሴን ተምሬ ተመልሼ የመምጣት ሃሳብ ነበረኝ። ወዲያው እንደተመለስኩ ግን የሕዳር ዐሥራ አራቱን ግድያ ስሰማ ተስፋ የጣልኩበት ለውጥ እንዳከተመ ገባኝ፡ ፡ እና በዚህ ወቅት የተሰማኝ ስሜት ፍፁም በሀገሬ ተስፋ መቁረጥና ኑሮዬን ባለሁበት መቀጠል ነበር። በዚህም ሙሉ ትኩረቴን ባለሁበት ሀገር ኑሮዬን የሚያሻሽሉ ነገሮች ላይ አደረግሁ። ነገር ግን ስለሀገሬ መፃፌን አላቆምኩም ነበር። ለምሳሌ ስለረሀቡ፣ በወቅቱ ስለነበረው አንባገነን መንግሥትና ስለመሳሰሉት ነገሮች በጥናት መልክ አድርጌ ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ይፋ አደርግ ነበር። በተለያዩ አጋጣሚዎች ስለ አፍሪካም ኾነ ስለኢትዮጵያ እጽፍ ነበር። አልፎ አልፎ ደግሞ ትምህርት ቤት ውስጥ ስለ አፍሪካ ወይም ስለ ኢትዮጵያ ክርክር ሲኖር ንግግር አደርጋለሁ ፤ እሳተፋለሁ።

ያም ቢኾን ግን በሀገሬ ተስፋ ቆርጬ ነበር፡ ፡ በወቅቱ ወታደራዊው መንግሥት በሀገሪቱ የሚፈፅመው ነገር የሕዝቡን ደህንነት ያልጠበቀ ከመኾኑ አንፃር ሕልሜ ሁሉ ኮስምኖ ተስፋ የምለው ነገር አልነበረኝም። የደርግን አካሄድ ሳየው ከዚህ በኋላ ጦርነት ድርቅ ረሃብ ነው የሚኖረው ብዬ ስላሰብኩ ለምን ብቻየን ለማልቀይረው ነገር እራሴን አሰቃያለሁ በሚል ራሴን እንዳገል አስገደደኝ። በኋላ ግን የህወሓት መንግሥት ሲገባ "አዲስ ሕገ መንግሥት ስለሚረቅ መጥተህ ተሳተፍ" የሚል ጥሪ ቀረበልኝ። እኔም ስለደረሰኝ ጥሪ ከቅርብ ጓዶቼ ጋር ከመከርኩ በኋላ አርቃቂው "አሸናፊው" ቡድን መኾኑን ስለተረዳሁ ጥያቄያቸውን ውድቅ አደረግኩት። በዚህ ሂደት ላይ እያለሁ ምርጫ 2005 (በእኛ 97) መጣ። በዚህ ወቅት እኔ ብቻ ሳልኾን ሁሉም ኢትዮጵያዊ አዲስ ተስፋ ሰንቆ ነበር ማለት ይቻላል። ለዚህ መነሳሳት ምንጩ ደግሞ በየሚዲያው የሚታየው የጋዜጠኛ ነፃነትና የፖለቲካ ክርክር ነበር።

ወዲያው ግን በምርጫው ዕለት ምሽት የህወሓት መንግሥት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አውጥቶ በሕዝቡ ላይ ነፃ የግድያ እርምጃ ሲወሰድ እኔም መናወጥ ውስጥ ገባሁ። ማለትም ሞቶ የነበረው የፖለቲካ ስሜቴ ተቀስቅሶ ድጋሚ ሲወርድ ለራሴ የማልፈታው ውዥንብር ውስጥ ገባሁ። በኋላ ግን በተለይም መርማሪ ኮሚሽን የሚባለው አካል የተገደሉትን ሰዎች ምስልና የግድያውን ዝርዝር ሁኔታ ይፋ ሲያደርግ ዝምታዬ ወንጀል ሆኖ ስለታየኝ መቃወም አለብኝ ብዬ ወሰንኩ። ነገር ግን በመቃወሜ እነሱን ማሸነፍ ባልችልም ሰላማቸውን መንሳት እንደሚቻል እምነት ስለነበረኝ በተቻለኝ አቅም የእነርሱን ወንጀልና ጥፋት ለማጋለጥ ወሰንኩ። በተለይም እነርሱ ዓለም ላይ ካላቸው ተቀባይነት አንጻር እኔ በብዕሬ በራስ መተማመናቸው ለመሸርሸር ተነሳሁ፣ ተሳክቶልኛል ማለት እችላለሁ። በዚህም በአንድ ወቅት አቶ መለስ በእኔ ላይ ያደረሰብኝ የግል በደል እንዳለና እንደሌለ እስከመጠየቅ ደርሶ እንደነበር አንድ ወዳጄ ነግሮኛል፡ ፡ አልፎም በተደጋጋሚ በጓደኞቼና በማስተምርበት ተቋም በኩል የተለያዩ መልዕክቶችን ይልክብኝ ነበር፡ ፡ እንደውም አንድ ወቅት የአገዛዙ ሰዎች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር የግል ስብሰባ እንድናደርግ ጠይቀውኝ ጭምር ነበር።



በሰዓቱ የእኔ መልስ "እንደ ግለሰብ ሳይኾን እኔም መሰሎቼን ይገፉ እርሳቸውም የሚመለከታቸውን የሥራ ባልደረቦች ይዘው በሀገሪቱ እያካሄዱት ያለውን የሰብዓዊ መብት ረገጣ የሚስተካከልበት ነገር ላይ እንወያይ" የሚል ነበር። ይኽ እንደማይኾን ሲነግሩኝ እኔም አቶ መለስን ማግኘት እንደማልሻ አሳወቅኳቸው። ነገር ግን አቶ መለስ 2010 ወደ አሜሪካ መጥቶ ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ ብዙዎች እዚህ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዳይናገር ሲረብሹት ነበር። እኔ ደግሞ የመናገር ነፃነቱን ልጋፋው አልፈለግሁም። በዚህም አንዳንዶች ተከፍሎት ነው" የሚል አሉባልታ እስከማስነገር ደርሰው ነበር። ያም ኾነ ይኽ እኔ ያገዛዙን ሽፍጦች በጽሑፌ አጋልጥ ነበር።

*ግዮን፡- የተለያዩ ጦማሮችን በተከታታይ መጻፍ የጀመሩት በዚህ ጊዜ ነበር ማለት ነው?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- መጻፍ የጀመርኩት ህወሓት ሥልጣን እንደያዙ ከ1990ዎቹ አንስቼ ነው። በወቅቱ እንደውም "ሃሳብ ይቀይራሉ፣ ዕድል ይሰጣቸው" የሚል ዐይነት ይዘት ያለውን ሃሳብ አንፀባርቅ ነበር፡ ፡ "ከመፈረጅ እንውጣ፣ ሥራቸውን እንይ" የሚል እምነትም ነበረኝ። በኋላ ግን በተለይም ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ በጽኑ መቃወም ጀመርኩ። ያው እኔ ጦር እየመሩ ጫካ መግባት ስለማላውቅ ባለኝ እውቀት መሟገት አለብኝ የሚል ውሳኔ ላይ ደረስኩኝ። በዚህም እነዚህን ሰዎች "international court of public opinion" ፊት አቅርቤ በየሳምንቱ ክስ እመሰርትባቸዋለሁ የሚል እምነት በአዕምሮዬ ቀረጽኩ። በመኾኑም የእነዚህን ሰዎች አዕምሮ ለመግራትና ለማሸነፍ ዘመቻዬን ጀመርኩ። በዚህም በተለይም ጽሑፎቼ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ገፅታ ባላውቅም በውጭው ዓለም ግን ራሳቸውን የቻለ ሚና ነበራቸው። የምዕራባውያንን ትኩረት በመሳብና በዲፕሎማት ደረጃ ያሉትን ከማባነን አኳያ የነበራቸው ስፍራም ቀላል አልነበረም። ኢትዮጵያ ውስጥ ከገባሁ በኋላ ግን በተለያየ መልኩ ጽሑፎቼን በርካቶች እንዳነበቡት መታዘብ ችያለሁ።

*ግዮን፡ ጽሑፎችዎ ዘወትር ቅዳሜ ነበር የሚወጡት?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- አዎ በአሜሪካ ቅዳሜ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ሰኞ ጠዋት ነው።

*ግዮን፡- ረጅም ዓመት በየሳምንቱ ጽፈዋልና መረጃዎቹን ከየት ነው የሚያመጧቸው? አሁንስ በዚያው መልኩ እየፃፉ ነው? አገኘሁበት የሚሉትስ ትርፍ አለ?*

ፕ/ር አለማየሁ፡- እንደሚታወቀው እኔ የሕግ ሰው ነኝ። እነዚህን ሰዎች ደግሞ ከፍ ሲል እንዳልኩት በየሳምንቱ በ "international court of public opinion" መክሰስ አለብኝ። በመኾኑም ለዚህ ሳምንታዊ ክስ ስል ማስረጃዎችን በየትኛውም መልኩ ማዘጋጀት አለብኝ። አንድ ጽሑፍ ከነማስረጃው ለማዘጋጀት ከ5 ሰዓት በላይ አይወስድብኝም፡ ፡ ማስረጃዎችን ከተለያየ ቦታ አገኛለሁ። የአገዛዙ ሰዎችም መረጃዎቹን ይልኩልኝ ነበር። ያገኘሁትን ውጤት በተመለከተ መለካት ባይቻልም በወቅቱ በነበረው መንግሥት ላይ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ እንደሚያሳርፍ ግን የተለያዩ ዲፕሎማቶችና አካላት ነግረውኛል። በተለያየ አጋጣሚ ከአምባሳደሮች ጋር ስገናኝ የጽሑፌን በሳልነትና የሰላ ተችነት ይነግሩኝ ነበር። በተጨማሪነት ህወሓት ለእኔ ጽሑፍ አንዴም ምላሽ ሰጥቶ አያውቅም። ያ ደግሞ የሚያመለክተው ጽሑፌ በመረጃ የተደገፈ ስለኾነ እርሱን ለማስተባበልና ለማውገዝ የሚያስችል ሁኔታ ላይ አለመኾናቸውን ነው ማለት ይቻላል።

በእርግጥ አንዳንድ የህወሓት/ኢሕአዴግ አፈቀላጤዎች የኔ ጽሑፍ ወጥቶ ሦስትና አራት ሳምንት ካለፈው በኋላ የተወላገዱ ማስተባበያዎችን ለመስጠት ሞክረው ነበር። ይኼ ደግሞ ወቅታዊነቱን ያልጠበቀና የተወናገረ ሃሳብ ከመሆን ያለፈ አልነበረም። እንደውም በህወሓቶች በኩል መጀመሪያ ጽሑፍ እንደጀመርኩ ሰልችቶት ይተዋል የሚል እምነት ነበራቸው። ኋላ ግን በቋሚነት ስቀጥል ከላይ እንዳልኩህ ከአፈቀላጤዎቻቸው በዘለለ ቀጥረው ምላሽ ለማጻፍ ቢሞክሩም አልተቻላቸውም፡ ፡ በዚህ መልኩ ትቀጥላለህ ወይ የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ አዎ እቀጥላለሁ። ለምሳሌ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ከስድስት በላይ አርቲክሎችን አውጥቻለሁ። ስለዚህ እቀጥልበታለሁ። በሌላ በኩል ጽሑፎቼን በተመለከተ አንድ አሜሪካን ኤምባሲ የሚሰራ ሰው ነበር። ይኽ ሰው የእኔን ጽሑፍ በተመለከተ ስጠይቀው ሥራዎቼ ፋይል እየተደረገ ወደ ስቴት ዲፓርትመንት መላካቸውን ነገረኝ።

*ግዮን፡- HR 2003 ሎቢ በማድረግ በኩል ዲፕሎማቶችን ለማናገር ፕ/ር አለማየሁ ትልቅ*

**ኃላፊነት ተወጥተዋል የሚሉ ወገኖች አሉና እርሶ በዚህ ዙሪያ ምን ይላሉ?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- መጀመሪያ ጭፍጨፋው ከተፈጸመ በኋላ ሕዳር አካባቢ ክሪስ ሚት የሚባል የሪፐብሊካን ሴናተር ከኒውጀርሲ አዲስ አበባ መጥቶ አቶ መለስን ስለምርመራ ሁኔታው ያናግረውና መለስ “ውጣልኝ” ብሎ ያባርረዋል፡፡ ይኽ ሰውየ አሜሪካ ይሄድና ኢትዮጵያ ውስጥ ስለነበረው ጭፍጨፋና ሰብዓዊ መብት ረገጣ ረቂቅ ማውጣት ይጀምራል፡፡ ሪፐብሊካኖቹ ሥልጣን ሲያጡ እርሱ ቦታውን በመልቀቁ ጀንዋል ፔን የሚባል ግለሰብ ጉዳዩን ያዘው፡፡ የዚህ ረቂቅ ስያሜው “Ethiopia Democracy Accountability” ይባላል፡፡

በዚህ ላይ ያሉት ዋና ሃሳቦች በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት መርምሮ ለፍርድ ማቅረብ፣ ትክክለኛ ምርጫ እንዲደረግ የምርጫ ሂደቱን ማከናወኛ የአሜሪካ መንግሥት በገንዘብ እርዳታ እንዲያደርግ ማስቻል፣ ሀገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲጠበቁ ማድረግ ወዘተ… የሚሉ ነበሩ፡፡ እንግዲህ እኔ በዚህ ላይ የተሳተፍኩት አንደኛው አሜሪካ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖችን ስለሕጉ ማስተማርና የተለያዩ ተሳትፎዎችን እንዲያደርጉ መቀስቀስ ሲኾን፣ ኹለተኛው ደግሞ በኮንግረስ ውስጥ አማካሪዎችን፣ ሴናተሮችንና ስቴት ዲፓርትመንት ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማናገርና በጽሑፍ መስጠት አልፎም በተለያየ አጋጣሚ መጎትጎትና ስለጉዳዩ ትኩረት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በዘለለ ደግሞ ጉዳዩን በጋዜጦችና በተለያዩ ዐውዶች ላይ በመጻፍና በማስተጋባት ነው፡፡

በአጠቃላይ የጭፍጨፋ ሁኔታውን ሁልጊዜ በተገኘው አጋጣሚ ወደ አደባባይ ማውጣትና ሰው እሱን ብቻ እንዲያወራ ማድረግ ነበር፤ ዋናው ዓላማ፡፡ ምክንያቱም ይኽን በማድረግ የወያኔ መንግሥት ላይ ትልቅ ቀውስ መፍጠር ይቻላል፡፡ ቀደም ሲልም ያላቸው ተቀባይነት የወረደ ስለኾነ በዚያው ልክ ተሰሚነት እንዳይኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የእኛ የቅስቀሳ ሂደት በዚህ ልክ እየገፋ እያለ የ2002(በኢትዮጵያ) ምርጫን አድርገው መቶ በመቶ አሸነፍን አሉ፡፡ ወዲያው የኦባማ መንግሥት አሜሪካ ላይ ተሰየመ፡፡ ይኽ መንግሥት ደግሞ ቅልጥ ያለ የወያኔ ደጋፊ ነበር፡፡ እናም በኦባማ ላይ ጫና እንዳናሳድር እርሱም ጥቁር ስለነበር በብዙ መልኩ ተወጥሮ ተይዞ ነበር፡፡ ወያኔዎችም የአልሻባብን መከሰት እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ከኦባማ መንግሥት ሚሊዮን ዶላሮችን መቀበል ቻሉ፡፡

በእኛ በኩልም ይኼን እንቅስቃሴ ይመሩት የነበሩ የተደራጁ ወገኖች ተስፋ በመቁረጥ መቀጠል ሳይቻላቸው እየተንጠባጠቡ ቀሩ፡፡ እኔም በግሌ በተለመደው መልኩ በጽሑፍ ቀጠልኩ፡፡ ምክንያቱም እኔ ያቅሜን ማድረግ ከቻልኩ ሌሎችም ፈለጌን ተከትለው የራሳቸውን አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፡፡ ያን የማያደርጉ ከኾነም በራሳቸው ነፃነትና ሕልውና ላይ እየቀለዱ ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ነፃነት ዝም ብሎ የሚገኝ ሳይኾን ሁሉም በየፊናው መራር ትግል አድርጎ የሚጎናፀፈው የሰብዓዊነት ጥግ በመኾኑ ነው፡፡

**ግዮን፡- እርሶ የህወሓትን መንግሥት እንዴት ይገልፁታል? በውድቀቱስ የተሰማዎት ስሜት እንዴት ይገለፃል?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እኔ ወያኔ እንደሚወርድ ተንብዬ ነበር፡፡ ይኽን ትንቢት 2013 በፃፍኩት ጽሁፍ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡ በታላቁ መጽሐፍ “የራሱን ቤት የበጠበጠ ግለሰብ ንፋስ ይዘግናል” የሚል ጥቅስ አለ፡፡ እኔም ህወሓቶችን ያልኳቸው “የኢትዮጵያን ቤት በጥብጣችኋልና መጨረሻችሁ ነፋስ ወይም ጉም መዝገን ነው የሚሆነው” ብዬ ተንብየላቸው ነበር፡፡ “ሁልጊዜ በጭፍጨፋና በዘረፋ እንኖራለሁ ብላችሁ አታስቡ በታሪክ ብዙ ጨፍጫፊና አንባገነኖች መጥተዋል፣ መጨረሻቸው ግን እጅግ አስከፊ አፈራረስ ነው፡፡ ስለዚህ ስህተታችሁን አርሙና ወደ ትክክለኛው መስመር ተመለሱ” የሚል ምክርም ለግሼ ነበር፡፡ ነገር ግን በታሪካቸው እድሉን አግኝተው ያልተጠቀሙ ብቸኞቹ አንባገነኖች ናቸው፡፡ በዚያ ጽሑፌ ስለኢትዮጵያ ትንሳኤ ሌላም የጠቀስኩት ነገር ነበር፡፡ “ለኢትዮጵያ ትንሳኤ የሚኾኑት ወጣቶች ናቸው” በማለት፡፡ የእኛ ትውልድ ከስሟል፣ ነገር ግን ወጣቶች ናቸው ኢትዮጵያን የሚድኗት፣ አንድ ወጣት ይመጣል ሀገሪቱን የሚታደጋት ብዬ ተናግሬም ነበር፡፡ እናም ከኹለት ዓመት በፊት ዶ/ር ዐቢይ ወደ ሥልጣን ሲመጣ እኔ ብዙ አልገረመኝም፡፡ ይኽ ማለት ደግሞ አውቃለሁ ማለቴ ሳይኾን ፖለቲካውን በአንክሮ ለተከታተለ ሰው ይኽ እንደሚኾን እንደማይጠፋው ለመግለጽ ነው፡፡

ዶ/ር ዐቢይ የተሾመና ቃለ-መሀላ የፈፀመ ዕለት ቪኦኤ ቃለ መጠይቅ አድርጎልኝ ነበር፡፡ እዚያ ቃለመጠይቅ ላይ የተናገርኩት ከፍ ሲል እንደጠቀስኩት “ይመጣል ያልኩት ሰው ይኼ ነው፣ የኢትዮጵያን ትንሳኤ የሚያሳየን እርሱ ነው” የሚል ነበር፡፡ ዶ/ር ዐቢይን ከዚያ በፊት በፍፁም አላውቀውም ነበር፡፡ በተጨማሪም በቃለ መጠይቁ ላይ ዐቢይን መቶ በመቶ እንደምደግፈው ተናግሬ ነበር፡፡ ዐቢይ በተሰየመ በስድስተኛው ቀን ላይም ይኽንኑ ድጋፌን የሚገልጽ ጽሑፍ አውጥቻለሁ፡፡

“በርታ፣ ወደፊት ሂድ፣ ቀጥልበት” የሚል ይዘት ያለው ጽሑፍ ነው፡፡ ስለዚህ የህወሓት ወያኔ መንግሥት ወደቀ የተባለ ግዜ በአዕምሮዬ በቂ ግንዛቤ ስለነበረኝ ብዙ አልደነቀኝም፡፡ ነገር ግን በወቅቱ የእነርሱ በሰላም መሰናበት በጣም ነበር ያስደሰተኝ፡፡ ትናንትም ኾነ በይበልጥ ደግሞ ዛሬ የህወሓት መንግሥትን የማየው በአሸባሪነት ነው፡፡ ይኼን ስል ዝም ብዬ ሳይሆን ድርጅቱ(ህወሓት) “Global Terrorism Data Base” በሚለው መዝገብ ላይ የተመዘገበ ስለሆነ ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ድርጅቱ እኔ አሸባሪ ስለው እነርሱን ለማጥላላት ፈልጌ ሳይሆን መሠረታዊ መረጃን በመያዝ ነው፡፡ የህወሓትን ማንነት ሥራው ይገልጠዋል፡፡ አሁን እያደረጉ ያሉት ደግሞ ከአልሸባብ፣ ከቦኮሐራም፣ ከአይሲስ ወዘተ… የባሰ ድርጊት ነው፡፡ ስለዚህ ይኽ ድርጅት አሸባሪነት እውነተኛ መገለጫው ነው ማለት ነው፡፡

**ግዮን፡- እንደሚታወቀው ከለውጡ በኋላ በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊን የሀገሩ ልማት ተሳታፊ ለማድረግ በማለም “የዳያስፖራ ትረስት ፈንድ” ተቋቁሞ እርሶ ትልቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ የትረስት ፈንዱ እንቅስቃሴ ምን ያህል ውጤታማ ነው ማለት ይቻላል? ከመንግሥትስ ጋር በምን ዓይነት መልኩ እየሰራችሁ ነው?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- እ.ኤ.አ ነሐሴ 2018 ጠ/ሚኒስትሩ አሜሪካ መጡ፣ መጥተውም ከማክያቶ ቀንሳችሁ 1 ዶላር ብትሰጡ ለሀገር ይረዳል አሉ፡፡ እኔ በወቅቱ እንደተረዳሁት ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕለታዊ ገቢው ከአንድ ዶላር በታች ነው፡፡ ስለዚህ እኛ በውጭ ያለነው ዜጎች ከማኪያቶ ቀንሰን አንድ ዶላር ከፈልን ማለት እያንዳንዳችን የአንድ ሰውን ሕይወት ቀየርን ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሃሳቡ የሚደገፍ ነው፡፡ በሌላ በኩል ዳያስፖራው በፊት የሚታወቀው በመከፋፈልና በመናቆር ስለኾነ አንድ አሰባሳቢና አቃፊ ፕሮጀክት እንዲኖረን በማሰብ የተመሰረተ ነው፡፡ ምክንያቱም ለሀገር ልማት የራስን አስተዋፅኦ ለማበርከትም መሰባሰብ መልካም ስለኾነ ነው፡፡ ይኽ ፈንድ ውሃ ማስቀፈር ይችላል፣ ትምህርት ቤት መሥራት ይችላል፣ ወጣቶችን ሥራ ሊያስገባ ይችላል፣ ለሴቶች የሥራ ዕድል ሊፈጥር ይችላል… ብቻ በጥቅሉ ለበርካታ አገልግሎት ሊውል የሚችል ነው፡፡ ያው በዚህ መልኩ ቢጀመርም ጥሩ እየሄደ መጥቶ አሁን ላይ ወደ ሰባት ሚሊየን ብር አካባቢ ማሰባሰብ ችለናል፡፡ ባለፈው ለኮቪድም 1.2 ሚሊዮን ብር አካባቢ ሰጥተናል፡፡ አሁን በቅርቡ ደግሞ አምስት ፕሮጀክቶችን ፈንድ አድርገናል፡፡ ሌሎች ወደ 16 የሚጠጉ ፕሮጀክቶችን ደግሞ ወደፊት በሥራ ላይ እናውላለን የሚል እምነት አለኝ፡፡ እንደሚታወቀው ኮቪድ ከመጣ በኋላ ብዙ ነገር ተቀያይሯል፡፡ አገር ውስጥ ያለው ችግርም በዝቷል፡፡ ለምሳሌ ለተፈናቃይ አምጡ ይባላል፣ ለአንበጣ አምጡ ይባላል፣ ዜጎች ተጎዱ ሲባል አምጡ ይባላል፡፡ ችግሩ ከመብዛቱ አኳያ ትንሽ መዳከም አለ፡፡ አሁን ያለው ተግዳሮት ይኽ ብቻ ነው፡፡ በጥቅሉ ትረስት ፈንዱ በዚሁ ይቀጥላል፡፡ እዚህ ብቻ ሳይኾን አገር ቤትም ቦርድ አለን፡፡ በዚህም ተናብበን ለመሥራት እየጣርን ነው፡፡

**ግዮን፡- ቀረ የሚሉት ነገር ካለ ሃሳቦን አጠቃልለው እንዲነግሩኝ ዕድሉን ልስጦት?**

ፕ/ር አለማየሁ፡- በጥቅሉ እስካሁን በመንግሥት በኩል እየተካሄደ ያለው ነገር ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ መንግሥት ሕግን በማስከበር በኩል የሚያደርገው እንቅስቃሴ በሕዝቡ ዘንድ ሙሉ ድጋፍ እንዳለው ተገንዝቤያለሁ፡፡ ይኼ ደግሞ መቀጠል አለበት፡፡ በሌላ በኩል የመንግሥት ሕግ የማስከበር ዘመቻ በትግራይ ብቻ ሳይኾን በሌሎች አካባቢም ሊኾን እንደሚገባና ሕዝብም ድጋፍ ሊሰጠው እንደሚገባ ማስታወስ እፈልጋለሁ፡፡ ጥፋት በተፈጠረ ቁጥር ራስን ማስተማር መልካም ነው፡፡ ስለዚህ የኔ መልዕክት መንግሥት ከዚህ የተማረውን ነገር በተግባር መግለጥ አለበት የሚል ነው፡፡ እኔ የተማርኩት ለዚህ ሁሉ ጥፋት ሊያደርሰን የቻለው ከውጭ የመጣ ጦስ ሳይኾን ሀገር በቀል የጥላቻ በሽታ ነው፡፡ ለዚህ ያበቃን ከልባችን የሚመነጨው የጥላቻ መንፈስ ነው፡፡ ለዚህም መነሻው ሥልጣን ላይ ለመቆየት የሚደረገው ጥረት ውጤት ነው፡፡

ይኽ ነገር ደግሞ የሀገር ጠንቅ ስለኾነ የሃይማኖት አባቶች፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ የሲቪክ ማኅበራት ወዘተ… ከዚህ ትምህርት ወስደው ለትውልድ ትምህርት መስጠት መቻል አለባቸው፡፡ ከአሁን በኋላ መደረግ ያለበት በእኩልነት ላይ ተመስርተን ሀገራችንን መገንባት አለብን፡፡ ሕግም መከበር አለበት፡፡ የሕግ የበላይነትነም ሊጠበቅ ይገባል፡፡ የግለሰብ መብት ሊጠበቅ ይገባል፡፡ ሌላ ምርጫ የለም፡፡ ወጣቱ ላይ ያተኮረ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ወጣቱ ከስድሳ በመቶ በላይ ስለኾነ የምትገነባው አዲሷ ኢትዮጵያ በወጣቶች ሊኾን ይገባል፡፡ የኔ ትውልድ ኢትዮጵያን ያየበት መንገድ መጨረሻ ክሽፈት ነው፡፡

ስለዚህ የምትገነባው ኢትዮጵያ ከዚያ ትውልድ የእሳቤ ቅንብብ ውጭ በኾነ መልኩ በወጣቱ መኾን አለበት፡፡ የኢትዮጵያ የወደፊት እጣፈንታ ያለው በወጣቶቹ ላይ ነው፡፡ ሌሎቻችን ተሳፋሪዎች ነን፡፡ አሁን የተፈጠረውን ነገር ለማስወገድ በእኔ እምነት ወጣቱ የእኛ ትውልድ የሰራውን ሕገመንግሥት ቀድዶ መጣል ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በዘር ከተደራጀ ሕገመንግሥት የፀዳ አዲስ፣ አመቺና አካታች ሕግን ማርቀቅ ይኖርበታል፡፡ ለክልልና ለዘር እውቅና የነፈገ ሕግ ማርቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ይኽ ማለት ግን አዲሱ ሕግ ራስን ማስተዳደርን ያስቀራል ማለት አይደለም፡፡ በጥቅሉ ከልጊቁ ጀምሮ በዚህ ዙሪያ ጠንካራ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

ለምሳሌ የኢትዮጵያን ብልፅግና በተመለከተ እስካሁን ዳያስፖራው ያደረገው ነገር የለም፡፡ ዓለም ላይ ያሉ ትውልደ ኢትዮጵያውያን አንድ በመኾን የኢኮኖሚስቶች ማኅበር አላቸው፡፡ ማኅበሩ ግን ለኢትዮጵያ ብልፅግና የፈየደው አንዳች ነገር የለም፡፡ ስለዚህ ወደፊት ይኼ መቀየር አለበት፡፡ ሁሉም በየሙያው ለውጥ ማምጣት ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ በጥቅሉ የጥላቻ ነገሮች ሁሉ ተደምስሰው ሀገሪቱ በወጣቶች ወደፊት መራመድ ይኖርባታል የሚል መልዕክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

**ግዮን፡- ለነበረን ቆይታ በአንባቢያን ስም ከልብ እናመሰግናለን፡፡**